2021
2022

# የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ

## የመረጃ/የኢንፎርሜሽን መጽሔት

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Maryland

## መግቢያ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎች በተመደበላቸው የመኖሪያ አካባቢ ት/ቤት ወይም ባለባቸው ግላዊ ሁኔታ ምክንያት በተመደቡበት የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ይጠበቃል። ተማሪዎች ከአካባቢ ት/ቤት ወይም በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም IEP ሂደት ምክንያት ከተመደቡበት፣ በሚከተሉት መመዘኛዎች/መስፈርት መሠረት  ወደ ሌላ ት/ቤት ለመቀየር (COSA) ማመልከት ይችላሉ፡-

- የተለየ ችግር/እንግልት— ከተማሪዎች አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ወይም ስሜታዊ ደህንነታቸው ጋር ወይም ከቤተሰቦቻቸው በየግላቸው ወይም ከራሳቸው ግላዊ ሁኔታ ጋር የተያያዘ አዳጋች ልዩ ሁኔታ በትምህርት ቤት ምደባ መቀየር ምክንያት የሚቀንስ/የሚያጠብ ሁኔታ የሚፈጥር ከሆነ ለ COSA ማመልከት ይችላሉ።
- የቤተሰብ ወደሌላ ቦታ መዛወር— ቤተሰቦቻቸው በሞንትጐመሪ ካውንቲ ውስጥ ቦታ የቀየሩ ተማሪዎች በቀድሞ ትምህርት ቤታቸው ትምህርታቸውን ለመቀጠል የሚፈልጉ ከሆነ የተለየ ችግር ምክንያት ሳያቀርቡ COSA መጠየቅ ይችላሉ። እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች ለወቅቱ የትምህርት ዘመን ቀሪ ጊዜ ብቻ ሊቀርቡ ይችላሉ፤ ከዚህ በተለይ በ 11ኛ ወይም 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው እስከሚመረቁ እንዲቆዩ COSA ይሰጣቸዋል።
- ወንድምና እህት—ተማሪው(ዋ) ወንድም ወይም እህት ወደሚማሩበት ትምህርት ቤት በመደበኛ/አጠቃላይ የትምህርት ቤት ፕሮግራም ወይም በልዩ ትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ለመካፈል ሲፈልግ/ስትፈልግ።
  - » ወንድም ወይም እህት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማግኔት፣ የቋንቋ ኢመርዥን፣ የሚማሩ ከሆነ ወይም ሌላ በማመልከቻ ፕሮግራም ላይ የሚገኙ ወንድሞችና እህቶችን እንደየጉዳዮ ሁኔታ COSA በቋሚነት ወደሚሰጠው የትምህርት ቤት ፕሮግራም እንዲገቡ ሊፈቀድላቸው ይችላል። የዚህ አይነት ፈቃድ በመማርያ ክፍል ቦታ የመኖር፣ የክፍል-ደረጃ ምዝገባ፣ የሰራተኛ አመዳደብ፣ ወይም በሚመለከታቸው ት/ቤቶች ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ታሳቢዎች ግንዛቤ ዉስጥ መግባት አለባቸው።

ከዚህ በላይ የተገለጸው ስለ ወንድም/እህት የተጠቀሰ መስፈርት የወሰን/ድንበር ለውጥ በሚደረግበት ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም።

እነዚህ ተማሪዎች ሌላ ትምህርት ቤት የሚጠይቁት በራሳቸው CONSORTIUM ከሆነ COSA እንዲያቀርቡ አይጠበቅባቸውም፡-

- በሰሜን ምስራቅ ክልል ዞርያ/Northeast Consortium (NEC) ወይም በታችኛው ካውንቲ ክልል ዞርያ Downcounty Consortium (DCC) የሚኖሩ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሌላ ክልል/Consortium ት/ቤት የሚጠይቁ ከሆነ።
- በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማግኔት ኮንሰርሽየም/Middle School Magnet Consortium (MSMC) የሚኖሩ የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች ወደ ሌላ የመካከለኛ ደረጃ ማግኔት ኮንሰርሽየም "MSMC" የሚጠይቁ ከሆነ ወይም በ MSMC የምልመላ ሂደት እጣ የተሳተፉ እና ለ MSMC ትምህርት ቤት የሚያመለክቱ ተማሪዎች።

በኮንሰርሽየም (CONSORTIUM) ከሚገኙት ትምህርት ቤቶች ወደ ሌላ ለመዛወር የሚጠይቁ ከሆነ፣ በጽሑፍ ተዘጋጅቶ የተፈረመበት ደብዳቤ ለ፡- Division of Consortia Choice and Application Program Services (DCCAPS) በኢሜይል DCCAPS@mcpsmd.org አድራሻ፡- 11721 Kemp Mill Road, Silver Spring, Maryland 20902 ማቅረብ አለብዎት  በ NEC፣ DCC፣ ወይም MSMC ትምህርት ቤቶችን ስለመቀየር መረጃ DCCAPS በስልክ ቁጥር 240-740-2540 ማግኘት ይችላሉ፥ ወይም ይህንን ድረገጽ ይጎብኙ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/schoolchoice።

እባክዎ ያስታውሱ፡- COSA ን ከተቀበሉ ወላጅ ወይም ሞግዚት መጓጓዣ/ትራንስፖርት መስጠት አለባቸው።

• ተማሪ በሞግዚትነት የሚያስተዳድሩ ሠራተኞች እና የእንክብካቤ አገልግሎቶች ክፍል (DPPAS)
240-740-5620 ፋክስ፡- 301-279-3971

# በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

## ት/ቤት ለመቀየር እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

MCPS FORM 335-45፣ Request for Change of School Assignment፣በዚህ መጽሔት አባሪ ተደርጓል። በተጨማሪ ቅጹ/ፎርሙ በዚህ ድረ-ገጽ ላይ www.montgomeryschoolsmd.org/info/transfers/ በስድስት ተጨማሪ ቋንቋዎች ይገኛል። ቅጹን ሞልተው የመኖርያ ማረጋገጫና ለፊርማ በርእሰ መምህር እንዲታይ ወደ አካባቢዎ ት/ቤት ያቅርቡ። ት/ቤቱ ቅጹን/ማመልከቻውን ለማካሄድ(ለማስፈጸም) ወደ DPPAS ይልካል።

ለት/ቤት ስርአት አዲስ የሆኑ ተማሪዎች የ COSA ጥያቄ ከማቅረባቸው በፊት በአካባቢያቸው ት/ቤት መመዝገብ አለባቸው። የ COSA ጥያቄዎች ተማሪው/ዋ የመኖርያ ማረጋገጫ እና የምዝገባ ሂደት በአካባቢ ት/ቤት እስኪ(ክት)ፈፅም ድረስ አይታዩም/አይገመገሙም።

## ማመልከት ያለብኝ መቼ ነው?

ለ 2021–2022 የትምህርት ዓመት የ COSA ማመልከቻዎች መቅረብ ያለባቸው ፌብሩወሪ 2021 በመጀመሪያው የትምህርት ቤት ቀን እና ኤፕሪል 2021 በመጀመሪያው የትምህርት ቤት ቀን መሆን አለበት። ስለቀረቡት የ COSA ጥያቄ እስከ ሜይ 28/2021 ድረስ ለወላጆች/ሞግዚቶች እና ለተማሪዎች ውሳኔውን ለማሳወቅ የተቻለንን ጥረት እናደርጋለን። ኤፕሪል ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን በኋላ የቀረቡ የ COSA ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚኖራቸው ተማሪው(ዋ) በሞንትጎመሪ ካውንቲ አዲስ ነዋሪ ከሆነ(ች) ብቻ ነው ወይም ከኤፕሪል በፊት ሊታሰብ የማይችል ድንገተኛ-አስቸኳይ የተከሰተ ሁኔታ ካለ ብቻ ነው። ይህን ሁኔታ የሚደግፍ ማስረጃ መቅረብ አለበት። COSA አመልክተው ዉሳኔ በመጠበቅ ላይ ያሉ/የሚጠባበቁ ተማሪዎች የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በተመደቡበት ት/ቤት መከታተል አለባቸው።

## ለ COSA ሳመለክት በአባሪነት ማቅረብ ያለብኝ ማስረጃዎች ምንድናቸው?

በእርስዎ ግላዊ ሁኔታ ይወሰናል፣ ነገር ግን፣ ሰነዶች በተናጥል ሊረጋገጡ የሚችሉ እውነታዎችን መያዝ አለባቸው። ለምሳሌ፡- የፋይናንስ ማስረጃዎችን፣ ከጤና ባለሙያዎች የተጻፉ ደብዳቤዎች፣ እና ከአሠሪዎች/ቀጣሪዎች የሚጻፉ ደብዳቤችን ያካትታል። እንደዚህ ዓይነት ሰነዶች በሌሉበት ሁኔታ፣ እንደዚህ ያሉ የተጋነኑ/አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የሚያሳይ ማስረጃ ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በመመካከር ማግኘት ይቻላል።

## ልዩ ችግር ማለት ምንድን ነው?

ልዩ ችግር በቤተሰብ ግላዊ እና ግለሰባዊ ሁኔታ ላይ የሚመሰረት ነው። በአብዛኞዎቹ ቤተሰቦች ዘንድ የጋራ የሆኑ ችግሮች፣ ለምሳሌ የህፃናት መዋያ/ዴይኬር፣ ወይም የፕሮግራም/የኮርስ ምርጫ፣ የመሣሡሉ ጉዳዮች ሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች ከሌሉ በስተቀር እንደ ከባድ ችግር-እንግልት ተደርገው አይቆጠሩም። ሁሉም የችግር ጥያቄዎች በተናጠል ሊረጋገጥ የሚችል ስነዳ ኣባሪ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፣ አለዚያ ጥያቄው ውድቅ ይደረጋል። እንደዚህ ዓይነት ሰነዶች በሌሉበት ሁኔታ፣ እንደዚህ ያሉ የተጋነኑ/አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የሚያሳይ ማስረጃ ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በመመካከር ማግኘት ይቻላል። እንደዚህ ያሉ የልዩ ችግር ምሳሌዎች፣ በዚህ የሚወሰኑ ባይሆንም የሚከተሉትን ያካትታል፡-

1. የልጅ እንክብካቤ፡- ወላጆች/ሞግዚቶች እድሜያቸው ለትም ህርት የደረሱ ተማሪዎች ከትምህርት ሰዓት በፊት ወይም ከትም ህርት ሠዓት በኋላ ለተማሪዎቹ እድሜ የሚመጥን አይነት ሁኔታ ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ክትትል ማድረግ አለባቸው። (ሀ) የሥራ ሰዓታቸው በቤት አካባቢ ለሚገኙት ት/ቤቶች የልጆች እንክብካቤ ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ከሚሰጠው ዓይነተኛ ሰዓት በላይ ወይም በቀላሉ ሊደረስ ባቸው የሚችሉ የሕፃናት እንክብካቤ ፕሮግራሞች ላይ በእጅጉ የሚራዘም ይሆናል፤ እና/ወይም (ለ) ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረት ደግሞ ቤተሰቡ የልጆችን እንክብካቤ በሌላ መንገድ የማግኘት ችሎታቸውን ይገድባል ወይም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የተማሪዎችን ፍላጎት ይገድባል። የተጋነኑ/አስቸጋሪ ሁኔታዎቹ ከአንደኛ ደረጃ ባሻገር ላሉ ተማሪዎች እጅግ በጣም ወሳኝ/ትርጉም ያለዉ መሆን አለበት።
2. የተማሪን አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ወይም ስሜታዊ ደህንነትን ያካተቱ/የሚመለከቱ የተጋነኑ/አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲኖሩ። በዚህ ምክንያት COSAs የሚፈልጉ ወላጆች/ሞግዚቶች (ሀ) ከተማሪው(ዋ) አካላዊ፣ አእምሯዊ ወይም ስሜታዊ ደህንነት ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ባላቸው ወይም በትምህርት ቤቱ አካባቢ ከሚደርስባቸው ተፅዕኖ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ቀጣይነት ያለው ሕክምና ከጤና ባለሙያ የሚሰጥ ሰነድ ማቅረብ አለባቸው፤ እና/ወይም (ለ) ልዩ ጥንቃቄ የሚጠይቁ ሁኔታዎች (ለምሳሌ፡- ከተማሪው(ዋ) የአካባቢ ት/ቤት እና/ወይም ከወላጅ/ሞግዚት የሥራ ቦታ በርቀት የሚገኝ ቦታ ተደጋጋሚ የህክምና ቀጠሮዎች የሚኖሩ ከሆነ)።

## ልጄ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የማይሰጥ የልዩ ትምህርት አገልግሎት እየተከታተለ(ች) ቢሆንስ?

የእርስዎ ተማሪ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የማይሰጥ በግላዊ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ የትምህርት አሠጣጥ ፕሮግራሙ/ሟ (IEP) የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን እንዲያገኝ/ድታገኝ የሚጠይቅ ከሆነ፣ COSA ለመጠየቅ ከሚያቀርቧቸው ተገቢ ምክንያቶች በተጨማሪ ተማሪው(ዋ) በልዩ ፕሮግራም በመታቀፍ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን እያገኘ(ች) መሆኑን የሚገልጽ COSA ቅጽ/ፎርም መሙላት አለብዎት። በሁሉም ት/ቤቶች የማይገኙ ልዩ የትምህርት ኣገልግሎቶች በመቀበል ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የሚደረጉ ጥያቄዎችን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ከጁላይ 1 በኋላ ይደረጋሉ። የበለጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማግኘት እባክዎ፡- Department of Special Education Services at 850 Hungerford Drive, Room 230, Rockville, Maryland 20850 ወይም በስልክ ቁጥር 240-740-3900 ያነጋግሩ።

## የ MCPS ሥራ ባልደረቦች ተማሪዎች COSA በቀጥታ ይፈቀድላቸዋል?

አይደለም። ይሁን እንጂ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስትራቴጂያዊ የቅድሚያ ትኩረት ጋር በሚጣጣም ሁኔታ በ "Title I ትምህርት ቤቶች"፣ በኢኖቬሽን የትምህርት ቤት የቀን መቁጠሪያ ትምህርት ቤቶች፣ ወይም በፎከስ ትምህርት ቤቶች የሚሠሩ የትምህርት ቤት ሠራተኞችን ለማበረታታትና ለመደገፍ ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች በአንዱ ላይ የሚሠሩ ሠራተኞች በሚከተሉት ሁኔታዎች በሚሠሩበት ትምህርት ቤት እንዲሠማሩ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡-

a. ለመጪው የትምህርት ዓመት ባጀት ተመድቦ ሙሉ ጊዜ (FTE) የዓመት እረፍት ፈቃድ፣ ጡረታ፣ እና የጤና ጥቅማጥቅሞች የሚያካትት በሙሉ ጊዜ ሠራተኛነት ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች በአንዱ እንዲሠራ-እንድትሠራ የተመደበ(ች) ሠራተኛ፥ እና

b. የሥራ ባልደረባው(ዋ) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ በመሆን፣ ተማሪው(ዋ) ወደ MCPS ለመመዝገብ ብቁ የሚሆን-የምትሆን ከሆነ(ች)፣ እና

c. ጥያቄው የሥራ ባልደረባው(ዋ) በሥራ ላይ በሚሆንበት/በምትሆንበት ጊዜ ሁሉ ከልጆች እንክብካቤ እቅድ ጋር የተያያዘ ይሆናል።

ሰራተኛዉ(ዋ) በሚሠራበት/በምትሰራበት ትምህርት ቤት የተማሪው(ዋ) መመደብ ሰራተኛው(ዋ)ን ስራዉን(ዋ)ን አጥጋቢ በሆነ መንገድ የማከናወን ችሎታዉ(ዋ)ን የሚያደናቅፍ ከሆነ፣ የተማሪ ዝውውሩ እንደገና ሊታገድ ይችላል።

በዚህ ክፍል ከተገለፁት ትምህርት ቤቶች በአንዱ የማይሰሩ የ MCPS ሰራተኞች በዚህ ፖሊሲ እና ተዛማጅ ህጎች መስፈርቶች መሰረት ለልጆቻቸው ለ COSAs ማመልከት ይችላሉ።

- **የዝውውር ሂደቱ ለጥንድ የአንደኛ ደረጃ/ኤሌሜንተሪ ት/ቤቶችም ተመሳሳይ ነው ወይ?**
አዎን። ተማሪው(ዋ) በ COSA የፀደቀ ጣምራ የትምህርት ፕሮግራም በ (Bel Pre፣ Montgomery Knolls፣ New Hampshire Estates፣ Roscoe R. Nix፣ Rosemary Hills፣ እና Takoma Park የኤለመተሪ ትምህርት ቤቶች) የሚከታተል/የምትከታተል ከሆነ(ች)፣ ላእላይ የኤለመንተሪ ክፍሎች ት/ቤት እንዲፀድቅላቸው የ COSA ቅጽ ሞልተው ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

- **ወደ ፑልስቪል ኤለመንተሪ ት/ቤት** (Poolesville Elementary School) **የተመደቡ እና ሞኖከሲ ኤለመንተሪ ት/ቤት** (Monocacy Elementary School) **ለመከታተል የሚፈልጉ ተማሪዎች አካሄዱ እንዴት ነው?**
ወላጆች/ሞግዚቶች እንዲፀድቅላቸው የ COSA ቅጽ ማቅረብ አለባቸው።

- **COSAዎች ለአካደሚዎች፣ የፊርማ/signature ፕሮግራሞች፣ ወይም ለልዩ ኮርሶች ይፈቀዳሉ ወይ?**
የለም። የፊርማ/signature ፕሮግራሞች እና ልዩ ኮርሶች ለሚገኙበት ት/ቤት ነው የተተለሙት። ወደነዚህ ት/ቤቶች የሚደረጉ የCOSA ጥያቄዎች ከሁሉም ሌሎች የCOSA ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። ከ COSA ሒደት ነጻ የሚሆኑ ፕሮግራሞችን በዚህ መጽሔት ገጽ 2-3 ይመልከቱ።

- **ተማሪዎች ለአካደሚያዊ ዝውውር የ COSA ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ?**
የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ከሚከተሉት በአንዱ ለመሣተፍ አካደሚያዊ ዝውውር ጥያቄ ለማቅረብ ይችላሉ፡-

1. በዲስትሪክቱ ወይም በትምህርት ቤት የኮርስ ካታሎግ ዝርዝር ውስጥ እንደተገለጸው በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ት/ቤት ውስጥ የማይገኙ ተዛማጅ የሆኑ በተከታታይ ብዙ ዓመት ለሚወሰዱ ኮርሶች። ይህ ተዛማጅነት ያላቸው ኮርሶችን ቅደምተከተል ነውሙያዊ የጥናት ፕሮግራም በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ት/ቤት የማይሰጡ የካፕስቶን ኮርስ እና/ወይም ፕሮግራም ማጠናቀቂያን የሚያመለክት ነው።

**ምሳሌዎች፡-**

በባለ ሙያ የሚመራ (ፕሮፌሽናል) የምግብ ቤት/ሬስቶራንት ማኔጅመንት ፕሮግራም፡- ተከታታዮቹ ኮርሶች የምግብ ቤት (ሬስቶራንት) ማኔጅመንት 1፣ የምግብ ቤት (ሬስቶራንት) ማኔጅመንት 2፣ እና ካፕስቶን ኢንተርንሽፕ ወይም ጣምራ ምዝገባን ያካትታሉ።

1. ሠርተፊኬት የሚሰጥበት የአበባ አትክልትና ፍራፍሬ ጥናት (ሆርቲካልቸር) ፕሮግራም፡- ተዛማጅነት ያላቸው ኮርሶች ቅደምተከተል የሚያካትተው፡- የአበባ አትክልትና ፍራፍሬ ጥናት (ሆርቲካልቸር)፣ የዕፅዋት ምርት፣ የመልካዓ ምድራዊ አጠባበቅ ንድፍ (ላንድሲፕ ዲዛይን)፣ እና ማኔጅመንት እንዲሁም የአካባቢ ጥናት ኢንተርንሽፕ ናቸው።
2. በተማሪው(ዋ) አካባቢ ትምህርት ቤት የማይገኝ ፣ በዲስትሪክቱ ወይም በት/ቤት የኮርስ ማውጫ ውስጥ እንደተገለፀው የበርካታ ዓመታት ተከታታይነት ያለዉ ነጠላ ኮርስ። ይህ የሚያመለክተው በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ት/ቤት ውስጥ ያልተሰጠ ለበርካታ ተከታታይ ዓመት በከፍተኛ ደረጃ ማጥናት የሚያስችል የስፔሻል ትምህርት ነው ።

**ምሳሌዎች፡-**
Arabic 1፣ Arabic 2፣ Arabic 3
Tap Dance 1፣ Tap Dance 2፣ Tap Dance 3

**ማሳሰቢያ፡-** በመጀመሪያው የት/ቤት ቀን መቅረብ አለበትፌብሩዋሪ 2021እና የመጀመሪያው የት/ቤት ቀን ኤፕሪል 2021። አመልካቾች ቦታ ካለ ይፈቀድላቸዋል። የእህትማማች/ወንድማማች ግንኙነት አይሠራም። ተማሪዎች ፕሮግራሙን ማቋረጥ ከፈለጉ፣ ወደ አካባቢያቸው ትምህርት ቤት ይመለሳሉ

- **ከ COSA መስፈርቶች ነፃ የሆኑ ፕሮግራሞች አሉ ወይ?**
የሚከተሉት ፕሮግራሞች የዝውውሩ አካል ያልሆኑ በማመልከቻ ሒደት ተደራሽነት ያላቸው ምሳሌዎች ናቸው፣ ነገር ግን፥ ሌላ የምልመላ መስፈርት ሊተገበር ይችላል።
  - አቪዬሽንና ኤሮስፔስ በ ኮ/ሎ ዛዶክ መግሩደር ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Aviation and Aerospace at Col. Zadok Magruder High School)
  - የኮሙኒኬሽን አርትስ ፕሮግራም በሞንትጎመሪ ብሌር ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Communication Arts Program at Montgomery Blair High School)
  - ሪጅናል ኢንተርናሽናል ባክልርዮት ዲፕሎማ ፕሮግራም በ ጆን ኤፍ. ኬኔዲ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Regional International Baccalaureate Diploma Program at John F. Kennedy High School)
  - ሪጅናል ኢንተርናሽናል ባክልርዮት ዲፕሎማ ፕሮግራም በ ስፕሪንግብሩክ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Regional International Baccalaureate Diploma Program at Springbrook High School)
  - ሪጅናል ኢንተርናሽናል ባክልርዮት ዲፕሎማ ፕሮግራም በ ዋትኪንስ ሚል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Regional International Baccalaureate Diploma Program at Watkins Mill High School)
  - ካውንቲ አቀፍ ሪጅናል ኢንተርናሽናል ባክልርዮት ዲፕሎማ ፕሮግራም በ ሪቻርድ ሞንትጎመሪ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Countywide International Baccalaureate Diploma Program at Richard Montgomery High School)
  - የአመራር ስልጠና ተቋም በ ጆን ኤፍ. ኬኔዲ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Leadership Training Institute at John F. Kennedy High School)
  - ሳይንስ፣ ሒሳብ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ ፕሮግራም በ ሞንትጎመሪ ብሌር ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤት (Science, Math, Computer Science Program at Montgomery Blair High School)
  - PLTW ምህንድስና ፕሮግራም በ ዊተን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (PLTW Engineering Program at Wheaton High School)
  - PLTW ባዮሜዲካል ፕሮግራም በዊተን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (PLTW Biomedical Program at Wheaton High School)
  - ቪዡዋል አርት ማእከል በአልበርት ኢንስታይን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Visual Art Center at Albert Einstein High School)
  - የጤና እንክብካቤ ሙያ በ ባዮሳይንስ አካደሚ በዊተን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በ ቶማስ ኤዲሰን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Healthcare Professions - Biosciences Academy at Wheaton High School and Thomas Edison High School of Technology)
  - የመስተንግዶ እና ቱሪዝም ማኔጅመንት በግሎባል ስተዲስ አካደሚ በዊተን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በ ቶማስ ኢድሰን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የቴክኖሎጂ ት/ቤት (Hospitality and Tourism Management - Global Studies Academy at Wheaton High School and Thomas Edison High School of Technology)
  - ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ሳይበር ሰኩሪቲ-አካደሚ ኦቭ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በ ዊተን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በ ቶማስ ኢድሰን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የቴክኖሎጂ ት/ቤት (Information Technology & Cyber Security - Academy of Information Technology at Wheaton High School and Thomas Edison High School of Technology)

- የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት እና ምህንድስና አካደሚ ኦቭ ኢንጅነሪንግ በ ዊተን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Construction Management and Engineering - Academy of Engineering at Wheaton High School and Thomas Edison High School of Technology)
- መካከለኛ ደረጃ ኮሌጅ በሞንትጎመሪ ኮሌጅ MC2ፕሮግራም በኖርዝውድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Middle College at Montgomery College (MC2) Program at Northwood High School)
- PLTW ባዮሜዲካል ሳይንስ IB ሙያዊ ፕሮግራሞች በ ሮክቪል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (PLTW Biomedical Sciences IB Career Programs at Rockville High School)
- PLTW ኢንጅነሪንግ IB ሙያዊ ፕሮግራሞች በ ሮክቪል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት(PLTW Engineering IB Career Programs at Rockville High School)
- የመስተንግዶ ማኔጅመንት IB ሙያዊ ፕሮግራሞች በ ሮክቪል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Hospitality Management IB Career Programs at Rockville High School)
- ኮድ.ኦርግ ኮምፒውተር ሳይንስ IB ሙያዊ ፕሮግራሞች በ ሮክቪል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት - (Code.org Computer Science IB Career Programs at Rockville High School)
- ግሎባል ኢኮሎጂ በ ፑልስቪል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Global Ecology at Poolesville High School)
- ሳይንስ፣ ሒሳብ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ ፕሮግራም በ ፑልስቪል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Science, Math, Computer Science Program at Poolesville High School)
- ሰብአዊነት (ሑማኒቲስ) በ ፑልስቪል ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Humanities at Poolesville High School)
- የጤና ጥበቃ ሙያ በ ሴኔካ ቫሊ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Healthcare Professions at Seneca Valley High School)
- መስተንግዶ እና ቱሪዝም ማኔጅመንት በ ሴኔካ ቫሊ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Hospitality and Tourism Management at Seneca Valley High School)
- ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ሳይበር ሰኩሪቲ በ ሴኔካ ቫሊ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Information Technology & Cyber Security at Seneca Valley High School)
- የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት እና አርኪቴክቸር በ ሴኔካ ቫሊ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Construction Management and Architecture at Seneca Valley High School)
- ፕሮጀክት ሊድ ዘ ዌይ ኢንጅነሪንግ በ ሴኔካ ቫሊ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Project Lead the Way Engineering at Seneca Valley High School)
- መካከለኛ ኮሌጅ በሞንትጎመሪ ኮሌጅ (MC2) ፕሮግራም በ ኖርዝዌስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Middle College at Montgomery College (MC2) Program at Northwest High School)
- PLTW ባዮሜዲካል ሳይንስ በ ጌትስበርግ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (PLTW Biomedical Sciences at Gaithersburg High School)
- ኔትዎርክ ኦፐሬሽንስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (PTECH) በ ክላርክስበርግ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Network Operations & Information Technology (PTECH) at Clarksburg High School)
- ሰብአዊነት - ሑማኒቲስ እና ኮሙኒኬሽን ማግኔት ፕሮግራም በ ኢንስተርን ሚድል ስኩል እና ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁንየር ሚድል ስኩል (The Humanities and Communication Magnet Program at Eastern Middle School and Dr. Martin Luther King, Jr. Middle School)
- ሳይንስ፣ ሒሳብ፣ እና ኮምፒውተር ሳይንስ ማግኔት ፕሮግራም በ ታኮማ ፓርክ ሚድል ስኩል እና ሮቤርቶ ክለመንቴ ሚድል ስኩል (The Science, Mathematics, and Computer Science Magnet Program at Takoma Park Middle School and Roberto Clemente Middle School)
- የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማግኔት ኮንሰርትዩም (Argyle፣ Loiederman፣ Parkland)
- ለዳበረ ትምህርት የጥናት ማእከሎች
- በማንኛውም የኤሌሜንታሪ ወይም መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራም የተመደቡ ተማሪዎች
- በት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የተለዩ ሌሎች ፕሮግራሞች
- ሌሎች ፕሮግራሞች አማራጮች/OPTIONS ላይ እንደተገለጸው፡
  - የካውንቲ አቀፍ ፕሮግራሞች መመሪያ/Guide to Countywide Programs (www.montgomeryschools.md.org/departments/enrichedinnovative/options)

ልዩ የሆነ ፕሮግራም ስለሚከታተሉ COSAs የፀደቀላቸው ተማሪዎች ከፕሮግራሙ የሚለቁ ከሆነ ወደ አካባቢያቸው ት/ቤት መመለስ ይኖርባቸዋል (www.montgomeryschoolsmd.org/departments/enrichedinnovative/ይመልከቱ ፡፡)

## የ COSA ጥያቄዬን ካቀረብኩ በኋላ ምን ሊሆን ይችላል?

በአካባቢ ት/ቤት ርእሰ መምህር/ት ከተፈረመበትና የመኖሪያ አካባቢ ከተረጋገጠ በኋላ፣ የ COSA ጥያቄ በዓመት ከ3,000 እስከ 4,000 ማመልከቻዎችን ለሚቀበለዉ ወደ DPPAS ይተላለፋል። ውሳኔ ከመሰጠቱ አስቀድሞ DPPAS መጣራት ያለባቸውን ነገሮች ያጠናቅቃል። አካደሚያዊ ዝውውር ከመጠየቅ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በሚመለከት፣ COSA ወደ "Office of Teaching, Learning" እና ለፕሮግራሙን የቀረቡትን ጥያቄዎች ወደሚገመግሙ ትምህርት ቤቶች በማስተላለፍ ከቤተሰብ ጋር ግንኙነት ይደረጋል።

## ጥያቄዬ መጽደቁን ወይም ውድቅ መደረጉን መቼ ነው የምሰማው?

ለወላጆች/ለሞግዚቶች እና ለተማሪዎች ከሜይ 28/2021 በፊት በፖስታ ለማሳወቅ የ DPPAS ሠራተኞች የተቻለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋሉ።

## ልጄ ለ COSA አንዴ ከተፈቀደለ(ላ)ት፣ በየአመቱ ማመልከት ያስፈልገኛል ወይ?

COSA የተወሰነው ለአንድ ዓመት ብቻ ካልሆነ በስተቀር፣ ተማሪው/ዋ ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ/እርከን ለመሸገር/ለመግባት ዝግጁ እስከሚ(ምት) ሆን ድረስ በ COSA ላይ ለመቆየት ይችላል/ትችላለች። በ COSA የኤለመንተሪ ት/ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ወደ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (ሚድል ስኩል) COSA ፕሮግራም ለመማር ያለባቸውን ልዩ አስቸጋሪ ሁኔታ በማረጋገጥ እንደገና ማመልከት ይኖርባቸዋል። በ 2021–2022 የትምህርት ዓመት ወደ 6ኛ ክፍል ከሚገቡ ተማሪዎች ጀምሮ፥ በ COSA ሚድል ስኩል (መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት) እየተከታተሉ የሚገኙ ተማሪዎች በዚያ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጋቢ በሆነ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለማር ከፈለጉ ያለባቸውን ልዩ አስቸጋሪ ሁኔታ በማረጋገጥ በድጋሚ ወደ COSA ማመልከት ይኖርባቸዋል። በ 2021-2022 ወደ 3ኛ ክፍል ከሚገቡ ተማሪዎች ጀምሮ በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኢመርዥን ፕሮግራም የሚገቡ ተማሪዎች ከአካባቢ ትምህርት ቤታቸው ውጪ ገብተው ለመማር  የዚያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጋቢ ከሆኑ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ጨምሮ COSA ለመጠቀም ማመልከት ይኖርባቸዋል።

## ልጄ ለCOSA ኣንዴ ከተፈቀደለ(ላ)ት፣ ውድቅ ሊደረግ ይችላል ወይ?

ኣንድ ርእሰመምህር፣ ለምሳሌ ቀጣይ የዲሲፕሊን ግድፈቶች ወይም የመከታተል/የመቅረት ጉዳዮች ካሉ፣ ኣንድን COSA ውድቅ እንዲሆን ሊ(ልት)ጠይቅ ይችላል/ትችላለች።

## በአዲሱ ት/ቤት ልጄ በት/ቤቶች የስፖርት ውድድር ለመጫወት ብቃት ይኖረዋል/ራታል ወይ?

በወቅቱ ከራሳቸዉ የመጋቢ ት/ቤት ዉጪ COSA የሚያገኙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አትሌቲክስ እንዲቀርላቸው ካላመለከቱ በስተቀር፣ በአትሌቲክስ ከመሣተፋቸው አስቀድሞ ለአንድ የካለንደር ዓመት በአዲሱ ት/ቤት መከታተል አለባቸው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት የአትሌቲክስ ዲፓርትመንትን በስልክ ቁጥር 240-740-5650 ይጠይቁ።

- **ወደ አዲሱ ት/ቤት ትራንስፖርት ይቀርባል ወይ?**
  አይደለም። የመጓጓዣ/ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የወላጅ/የሞግዚት ኃላፊነት ነው።

- **የኔ COSA ውድቅ ተደረገ። እንዴት አድርጌ ነው ይግባኝ የምለው?**
  በጽሑፍ ወደ፡- OFFICE OF OPERATIONS, 850 HUNGERFORD DRIVE, ROOM 43, ROCKVILLE, MARYLAND 20850 ማመልከት ይችላሉ። የሥራ አመራር ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንቱ(ቷ) ትምህርት ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ/ሱፐርኢንተንደንትን በመወከል ያገለግላል/ታገለግላለች። የውሳኔው ደብዳቤ ከደረሰበት ቀን አንስቶ ከ 15 የካለንደር ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ይግባኙ ወደ "Office of Operations" በጽሑፍ መድረስ ይኖርበታል። ውሳኔው እንደገና እንዲታይ ያስፈለገበትን ምክንያት(ቶች) ይግባኙ ላይ መገለጽ አለበት። ይግባኝ ለመጠየቅ ተጨማሪ ኢንፎርሜሽን መስጠት ላይኖርብዎት ይችላል፣ነገር ግን ቢታይ ይጠቅመኛል የሚሉትን ተጨማሪ መረጃ እንዲታይልዎት ለማቅረብ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር፡- 240-740-4130 ይደውሉ። የCOSA ይግባኝ ላይ ውሳኔ የሚጠባበቁ ተማሪዎች የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በተመደቡበት ት/ቤት ይከታተላሉ።

  ይግባኝ በሙሉ የሚታየው በቀረቡት ሠነዶች እና በክትትል ኮሚዩኒኬሽን/ግንኙነት ላይ ተመስርቶ ነው።

  እርስዎ ያቀረቡት አቤቱታ በሥራ አመራር ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት አማካይነት ውድቅ ከተደረገ፥ ለMONTGOMERY COUNTY BOARD OF EDUCATION (BOARD), VIA EMAIL BOEAPPEALS@MCPSMD.ORG, 850 HUNGERFORD DRIVE, ROOM 123, ROCKVILLE, MARYLAND 20850, በሥራ አመራር ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት ውሳኔ በደብዳቤ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በ 30 የካለንደር ቀናት ውስጥ ወይም ከዚያ ባነሰ ጊዜ በፍጥነት ይግባኝ እንዲያቀርቡ በአጽንኦት ይመከራል። ሁሉም ይግባኞች የሚሰሙት በቦርዱ መደበኛ የስብሰባ ቀኖች ነው። ቦርዱ በኦገስት ወር እረፍት ላይ እንደሚሆን እባካችሁ አስተውሉ።

ማሳሰቢያ፡- ከጁላይ 1/2021 በፊት ወደ ሥራ አመራር ጽ/ቤት "Office of Operations" ለቀረቡ ይግባኞች የትምህርት ዓመት ከመጀመሩ አስቀድሞ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል። ከጁላይ 1/2021 በኋላ ለደረሱ ይግባኞች የመጨረሻ ውሳኔ የትምህርት ዓመቱ ከተመጀመረ በኋላ ሊሰጡ ይችላሉ።

Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

MCPS ቅጽ 335-45
ጃኑወሪ 2021

# ከተመደቡበት ትምህርት ቤት ዝውውር ስለመጠየቅ (Change of School Assignment (COSA))

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS (MCPS)
Rockville፣ Maryland 20850

*መመሪያዎች፡- ወላጅ/አሳዳጊ የቅጹን ክፍል 1 በመሙላት ከኤፕሪል 2021 የመጀመሪያ የትምህርት ቀን በፊት ቅጹን ለአካባቢ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር ማስረከብ ይኖርባቸዋል። ቅጹን ከመሙላትዎ በፊት ከምድብ ትምህርት ቤት ዝውውር (Change of School Assignment (COSA)) የመረጃ መጽሔት ዉስጥ የሚገኘውን መረጃ በጥንቃቄ ያንብቡ። የትምህርት ቦርድ ፓሊሲ JEE ን ፣የተማሪ ዝዉዉሮች፣ እና የ MCPS ደንብ JEE-RA፣የተማሪ ዝዉዉሮች እና አስተዳደራዊ ምደባዎችን ይመልከቱ።*

የተማሪ ስም ______________________________________________ የትዉልድ ቀን ____/____/____
የመጨረሻ  መጠሪያ/መጀመሪያ  የመካከለኛ ስም (የአባት) መነሻ ፊደል

የስፔሻል ኢጁኬሽን አገልግሎቶችን ያገኛሉ  አይደለም ☐  አዎ ☐

አሁን የሚማርበት/የምትማርበት ትምህርት ቤት ______________________ ኦገስት 2021 የሚገባበት ክፍል _____

የአካባቢ ትምህርት ቤት ____________________ የተጠየቀው ትምህርት ቤት____________  የሚፈጸምበት ቀን____/____/______

ወላጅ/አሳዳጊ፡- ______________________________________________

አድራሻ፡- ______________________________________________
Street  City  State  Zip Code

የቤት ስልክ_______-_______-_________  የሥራ ቦታ ስልክ_______-_______-_________  ሞባይል ስልክ_______-_______-_________

የኢ-ሜይል አድራሻ ______________________________________________

ቤት ውስጥ የምትጠቀሙት ቋንቋ ______________________________________ TTY ያስፈልጋል ☐

ጥያቄ የቀረበበት ምክንያት፡-

- ☐ የተለየ ከባድ ሁኔታ—እባክዎ ዝርዝሩን ይግለጹ፣ የማረጋገጫ ሠነዶች ከዚህ ቅጽ ጋር መያያዝ አለበት።
- ☐ ቤተሰብ ወደሌላ ቦታ መዛወር— ቤተሰብ ወደሌላ ቦታ በመዛወሩ ምክንያት ይህንን የትምህርት ዓመት ማጠናቀቅ።
- ☐ ወንድም/እህት—ወንድም/እህት በተጠየቀው ትምህርት ቤት በ..ክፍል እየተማሩ ስለሚገኙ_____
  የወንድም/እህት ስም ______________________________የወንድም/እህት የ MCPS መታወቂያ ቁጥር _________________
- ☐ ከ3ኛ እስከ 5ኛ ክፍሎችን በ (ቤል ፕሬ/Bel Pre፣ ሞንትጎመሪ ኖልስ/Montgomery Knolls፣ ኒው ሃምብሻየር ኢስቴትስ/New Hampshire Estates፣ ሮስኮ አር. ኒክስ/Roscoe R. Nix፣ ሮዝመሪ ሂልስ/Rosemary Hills፣ እና ታኮማ ፓርክ/Takoma Park) የኤለመንተሪ ትምህርት ቤቶች በጣምራ ለመከታተል የመቀጠል ፍላጎት። (ቀደም ሲል የፀደቀ የ COSA ቅጽ/ፎርም ከቀረበ ወዲያውኑ ሊጸድቅ ይችላል)
- ☐ ከመካከለኛ ደረጃ (ሚድል ስኩል) እስከ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ (ሃይ ስኩል) ድረስ በመጋቢ ትምህርት ቤቶች አመዳደብ የመቀጠል ፍላጎት፣ የማካለል ለውጥ ካልተድረገ በስተቀር፣ ቀደም ሲል የፀደቀ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ሚድል ስኩል) COSA (የ COSA ጥያቄ ሲቀርብ ወዲያዉኑ የሚፀድቅ ካልሆነ- Automatic approval upon COSA form submission)እባክዎ ልብ ይበሉ፡- የዚህ ቀነገደብ የሚያበቃው፡-
  - ሀ/ በ 2021–2022 የትምህርት ዓመት ወደ 6ኛ ክፍል ለሚገቡ ተማሪዎች።
  - ለ) በ 2021–2022 የትምህርት ዓመት 3ኛ ክፍል ኢመርዥን ፕሮግራም ለሚገቡ ተማሪዎች።
- ☐ ወደ ፑልስቪል ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት (Poolesville Elementary School) የተመደበ(ች) ተማሪ በሞኖካሲ ኤለመንተሪ ትምህርት ቤት (Monocacy Elementary School) ለመማር የሚፈልግ-የምትፈልግ ተማሪ (የ COSA ቅጽ ሲቀርብ ወዲያውኑ ይፀድቃል)
- ☐ በ "Title I School፣ Innovative School Year Calendar School፣ ወይም Focus School" በመሥራት ላይ የሚገኝ-የምትገኝ የ MCPS ሠራተኛ፣ ልጃቸው እነርሱ ወደሚሠሩበት ትምህርት ቤት እንዲዛወር-እንድትዛወር የሚጠይቁ ከሆነ እርስዎ የሚሰሩበት/የተቀጠሩበት ትምህርት ቤት ስም
- ☐ የአካዳሚክ ዝውውር (ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ)የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ፕሮግራም እና የትምህርት ቤቱን ስም ይግለጹ የግምገማው ሒደት በተጠየቀው ትምህርት ቤት የቦታ እና በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ት/ቤት የፕሮግራም መገኘት-አለመገኘትን ግምት ውስጥ ያስገባል። ይበልጥ መረጃ ለማግኘት፣ ይጎብኙ፡- https://www.montgomeryschoolsmd.org/info/transfers/። የትምህርት ቤት አቅም፣ እና ስለፕሮግራም መገኘት" ይበልጥ መረጃ ለማግኘት

ስለ አካደሚክ ዝውውር እዚህ ክሊክ ያድርጉ።

ለ 2021-2022 የትምህርት አመት፣ የመጠየቂያ ፎርሞች በ2021 ፌብርዋሪ ዉስጥ ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን በኋላ፣ እና በኤፕሪል 2021 ከመጀመሪያዉ የትምህርት ቀን በፊት ገቢ መሆን አለባቸው። ያልታሰቡ/ልዩ ሁኔታዎች ካላጋጠሙ በስተቀር፣ ዘግይተው የደረሱ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር፣ ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ የተፈቀደዉ ትምህርት ቤት ከተማሪው/ዋ የመጋቢ ቅጥ/ስርዓት ውጭ መሆኑ ይገባኛል፡- 1) ትራንስፖርት በ MCPS እንደማይቀርብ፣ 2) ተማሪው/ዋ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሆነ/ች፣ በአትሌቲክስ ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ ከመሆን በፊት በአዲሱ ትምህርት ቤት አንድ አመት መከታተል አለበት/ባት (እንዲቀር/ዌይቨር ካልተፈቀደ በስተቀር)፣ እና 3) የተፈቀደዉ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር/ት የተማሪው/ዋ COSA በተገቢ ምክንያት እንዲሰረዝ ሊጠይቅ/ልትጠይቅ ይችላል/ትችላለች። (የ MCPS ደንብ JEE-RA ን ይመልከቱ)።

በዚህ ቅጽ እና በማናቸውም አባሪዎች ላይ የቀረቡት መረጃዎች እኔ እስከማውቀው ድረስ ትክክለኛ፣ የተሟሉ እና እውነት ናቸው። ማንኛዉንም ለ COSA የቀረበ ማስረጃ፣ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ማጭበርበር ከተገኘበት ውድቅ ለማድረግ ምክንያት እንደሚሆን ተረድቻለሁ።

ፊርማ፣ ወላጅ/አሳዳጊ/እድሜ የሚያሟላ/የምታሟላ ተማሪ ______________________________ ቀን ____/____/____

## ክፍል II፡- የትምህርት ቤት ግምገማ። በተማሪው/ዋ የአካባቢ ት/ቤት ርእሰ መምህር የሚሞላ።

የነዋሪነት ማረጋገጫ የተጠናቀቀበት  ቀን ____/____/______  የ MCPS ተማሪ መታወቂያ ቁጥር #________________

ይህንን ጥያቄ በሚመለከት ከወላጅ/ሞግዚት ጋር ተነጋግሬአለሁ  አዎ ☐  አይደለም☐  የትምህርት ቤት#_________

ፊርማ፣ ርእሰመምህር______________________________ ቀን ____/____/____

(መፈረም ማለት በቀረበው ጥያቄ ላይ ስምምነትን/አለመስማማትን ለማረጋገጥ ሳይሆን ነገር ግን ነዋሪነቱ(ቷ) የተረጋገጠ መሆኑን ብቻ ያመለክታል።)

ወደ ..ተላልፏል፡- Director, Division of Pupil Personnel and Attendance Services (DPPAS), 850 Hungerford Drive, Room 211, Rockville, MD 20850

## ክፍል III፡- DPPAS ACTION/የተወሰደ እርምጃ። በ DPPAS አማካይነት የሚሞላ።

ወደ..ተላልፏል፡- Consortium Office ☐  Special Education ☐  Date ____/____/______

የ DPPAS ውሳኔ/DPPAS Decision፡-

☐ ፀድቋል  ☐ የትምህርት ዓመቱ እስከሚያልቅ ድረስ፣ ፀድቋል _____  ☐ ተቀባይነት የለውም—ምንም በሠነድ የተረጋገጠ የተለየ ከባድ ሁኔታ የለም

አስተያየቶች፡-______________________________________________

ፊርማ፣ ዳይሬክተር ወይም አስተባባሪ፣ DPPAS______________________________ ቀን ____/____/____

ይግባኝ፡- ይግባኙ በ DPPAS ተቀባይነት ካላገኘ፣ (እባክዎ ምክንያቱን እና ማንኛዉንም ተጨማሪ መረጃና ማስረጃ ይግለጹ) ይህ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ 15 የካላንደር ቀናት ውስጥ ለ. Office of Operations , Montgomery County Public Schools, 850 Hungerford Drive, Room 43, Rockville, Maryland 20850. በፅሁፍ መቅረብ አለበት።

| | | |
|---|---|---|
| የዳወንካውንቲ ኮንሰርሽየም<br>DOWNCOUNTY CONSORTIUM<br>ሞንጎመሪ ብሌር (MONTGOMERY BLAIR)፣ አልበርት አንስታይን (ALBERT EINSTEIN)፣ ጆን ኤፍ ኬኔዲ (JOHN F. KENNEDY)፣ ኖርዝ ውድ (NORTHWOOD) ዊህተን (WHEATON)<br>የመካከለኛ ደርጃ ት/ቤት ማግኔት ኮንሰርሽየም<br>ARGYLE, A. MARIO LOIEDERMAN, PARKLAND | ኖርዝኢስት ኮንሰርሽየም<br>NORTHEAST CONSORTIUM<br>ጄምስ ሁበርት ብሌክ (JAMES HUBERT BLAKE)፣ ፔይንት ብራንች (PAINT BRANCH)፣ ስፐሪንግ ብሩክ (SPRINGBROOK)<br>11721 Kemp Mill Road<br>Silver Spring, Maryland 20902<br>240-740-2540<br>DCCAPS@mcpsmd.org | DEPARTMENT OF SPECIAL EDUCATION SERVICES<br>850 Hungerford Drive<br>Room 230<br>Rockville, Maryland 20850<br>240-740-3900 |

## የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎ መግለጫ

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ዘርን፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ የዘር ሃረግ፣ የብሄር ማንነት፣ ሃይማኖት፣ የስደተኝነት/የፍልሰተኝነት ሁኔታ፣ (ባይሎጂካል/ተፈጥሯዊ) ጾታን፣ (ተለምዷዊ) ስነ-ጾታ፣ የጾታ ማንነት (gender identity)፣ የጾታ አገላለጽ (gender expression)፣ የጾታዊ ግኑኝነት ዝንባሌ/ምርጫ (sexual orientation)፣ የቤተሰብ/የወላጆች (የኑሮ) ደረጃ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ እድሜ፣ ድህነት እና የማህበራዊ ኤኮኖሚያዊ አቋም፣ ቋንቋ፣ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኝነት፣ ወይም ሌሎች በህገመንግስት ጥበቃ የተደረገላቸውን ገጽታዎች/ባህሪያትን ወይም ትስስርን/ተዛማጅነት ያላቸውን (affiliations) መሠረት ያደረገን ሕገ-ወጥ መድሎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለማዳበር ሲደረግ የቆየውን ትጋት ይሸረሽራል/ያበላሻል። አድልዎ የሚከተሉትን የተወሰኑ ምሳሌዎችን ያካትታል፡ ጥላቻ፣ ሁከት፣ ደንታቢስነት፣ ወከባ፣ ማሸማቀቅ፣ ንቀት፣ ወይም መልሶ ማጥቃት። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ-Montgomery County Board of Education Policy ACA ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ/Nondiscrimination, ፍትሃዊነት/ሚዛናዊነት/Equity, እና የዳበረ ባህል/Cultural Proficiency. ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ የመሆኑ(ኗ)ን፣ በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ሃቀኛ ወይም የሚታሰብ ግላዊ ጠባዮች የሚተነበዩ አለመሆናቸውን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። መርሁ/ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው ርምጃዎችን የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግ፣ በተቋማት መዋቅሮች ላይ የሚፈጸሙ መሰናክሎች፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል።

| በ MCPS ሰራተኛ ስለደረሰ መድሎዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ለማቅረብ* | በ MCPS ተማሪዎች ላይ የአድልዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ካላችሁ* |
|---|---|
| የሰራተኛ ተሳትፎ እና የሥራ ግንኙነት ጽ/ቤት<br>አድራሻ፡-Department of Compliance and Investigations<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>OEELR-EmployeeEngagement@mcpsmd.org | Office of the Chief of Staff<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 162, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>COS-StudentWelfare@mcpsmd.org |
| በ "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፣ በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ መድሎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች፣ ጾታዊ ጥቃቶችን ጭምር* | |
| Title IX Coordinator<br>Office of the Chief of Staff<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 162, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>COS-TitleIX@mcpsmd.org | |

*የአካል ስንክልና ላላቸው ተማሪዎች ለመገልገያዎች የሚቀርቡ አቤቱታዎች፣ ቅሬታዎች ወይም ጥያቄዎች ወደ፣ በ Resolution and Compliance Unit ለ Office of Special Education ሱፐርቫይዘር/ተቆጣጣሪ የልዩ ትምህርት፣ መፍትሄ እና የአዎንታ ክፍል ፅ/ቤት፣ በስልክ ቁጥር 240-740-3230 ሊመሩ ይችላሉ። ሠራተኞችን የሚመለከቱ አኮሞዴሽን ወይም ይዘት የመቀየርና የማስተካከል ጥያቄዎች ወደ "Office of Employee Engagement and Labor Relations, Department of Compliance and Investigations, ስልክ፡- 240-740-2888 ይመራ ይሆናል። በተጨማሪም ስለ አድሎአዊነት ቅሬታ ለሚከተሉት ድርጅቶች ማመልከት ይቻላል፡- the U.S. Equal Employment Opportunity Commission, Baltimore Field Office, City Crescent Bldg., 10 S. Howard Street, Third Floor, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights, Lyndon Baines Johnson Dept. of Education Bldg., 400 Maryland Avenue, SW, Washington, DC 20202-1100, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

በጥያቄ ይህንን ዶኩመንት ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ እና በአማራጭ ቅርጸት Americans with Disabilities Act፣ የ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም በ PIO@mcpsmd.org ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ/ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ሰዎች የ MCPS Office of Interpreting Services በስልክ ቁጥር 240-740-1800፣ 301-637-2958 (VP) ወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org ለመጠየቅ ይችላሉ። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለወንድ/ለሴት ስካውቶች እና ሌሎችም የሚመለከታቸው የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነትን ይሰጣል።

Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

ሕትመት በ፡- Department of Materials Management for the Office of Operations
ትርጉም፡- በቋንቋ ድጋፍ አገልግሎቶች ክፍል • የኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት
Language Assistance Services Unit • Office of Communications
0238.21 • Editorial, Graphics & Publishing Services • 1/21 • NP
Copyright © 2020 Montgomery County Public Schools, Rockville, Maryland